ቁጥር 1

ስለኔ ማን ነኝ

ክፍል ለህፃናት

የሕፃናት ሕጋዊ ከለላ ማዕከል
Children's Legal Protection Centre

የአፍሪካ ሕፃናት ፖሊሲ መድረክ በህፃናት መብት ዙሪያ የሚሠራ አህጉር አቀፍ ድርጅት ሲሆን ዓላማውም የህፃናት ጉዳይ በመንግስት አጀንዳ በቀዳሚነት እንዲቀመጥ ግፊት ማድረግ ነው። መድረኩ የህፃናት መብትና ደህንነት መከበር በአፍሪካ ብሎም በዓለም ቀጣይና ዘለቂታ ያለው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማምጣት አስተዋፅኦ እንደሚያደርግ ያምናል። የመድረኩ ተግባር በዓለም አቀፋዊ እሴቶችና ተሞክሮች ላይ ተመርኩዞ የሰብዓዊ መብቶችን መከበርና መተግበር መሠረት ያደረገ ነው። መሠረታዊ ዓላማውም የአፍሪካ ህፃናት እየደረሰባቸው ያለውን ችግር በበለጠ ለማሳወቅ የመነጋገሪያ መድረክ መዘርጋት፣ አማራጭ የፖሊሲ ሀሳቦችን መጠቆምና መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አቅም በማጎልበት የህፃናትን ጥቅም ያስቀደሙ ፖሊሲዎች እንዲሁም ፕሮግራሞች እንዲወጡና በሥራ ላይም እንዲውሉ ማድረግ ነው።

መድረኩ የኢትዮጵያ ህፃናት መብቶቻቸው ተከብረውላቸውና ከጥቃት ተጠብቀው ያድጉ ዘንድ ነፃ የሕግ አገልግሎት እንዲያገኙ፣ ህብረተሰቡም ሆነ የሕግ አስፈፃሚ አካላት ለህፃናቱ መብት መከበር እንዲሰሩ ለማድረግ እንዲሁም ለህፃናቱ ደህንነት ምቹ ሕጎችና አሰራሮች እንዲኖሩ ማድረግ እንዲቻል ራሱን የቻለ ፕሮግራም ቀርጾ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ስለዚህም ድርጅቱ የሕፃናት ሕጋዊ ከለላ ማዕከልን በ1997 ዓ.ም. አቋቁሟል።

ማዕከሉ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ለበርካታ ህፃናትና ለቤተሰቦቻቸው የተለያዩ የሕግና የማህበራዊ አገልግሎቶችን ሰጥቷል። በተጨማሪም ጥቃት ለደረሰባቸው ህፃናት ከሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር የተለያዩ ማህበራዊ ድጋፎችን (እንደ ህክምና አገልግሎት፣ ጊዜያዊ መጠለያ፣ የትምህርት ድጋፍ ወዘተ) እንዲያገኙ አድርጓል። እንዲሁም ህብረተሰቡ፣ የፍትህ አካላትና የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች ስለህፃናት መብት በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ ስልጠናዎችን ይሰጣል። ማዕከሉ ቋሚ የሬዲዮ ፕሮግራም በማዘጋጀት እንዲሁም በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ፅሁፎችን በማሳተም ህብረተሰቡ ስለ ህፃናት መብት ያለው ግንዛቤ ከፍ እንዲል ጥረት ያደርጋል። ለህፃናት አመቺ የሆኑ ሕጎችና አሰራሮች እንዲኖሩ ለማድረግም የተለያዩ ጥናቶችን እያካሄደ የሕግና የአሰራር ለውጥ እንዲመጣ ግፊት ያደርጋል።

ይህንን ሕትመት እና ሌሎች በአፍሪካ ሕፃናት ፖሊሲ መድረክ የሚታተሙትን ሰነዶች ሁሉ ቀጥሎ በተገለጸው ድህረገጾች ላይ በቀጥታ ማግኘት ይቻላል።

www.africanchildforum.org ወይም www.africanchild.info

የአፍሪካ ህፃናት ፖሊሲ መድረክ
ፖ.ሣ.ቁ. 1179
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ስልክ ቁጥር +251-11-662-81-92
+251-11-662-81-96
+251-11-662-81-99
ፋክስ ቁጥር +251-11-662-82-00

ኢሜል info@africanchildforum.org

The African Child Policy Forum
የሕፃናት ሕጋዊ ከለላ ማዕከል

©2009 The African Child Policy Forum

የህፃናት ህጋዊ ከለላ ማዕከል
ፖ.ሣ.ቁ. 1179
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ስልክ ቁጥር +251-11-551-16-48
+251-11-550-29-97
+251-11-655-67-63/64
ፋክስ ቁጥር +251-11-553-55-42

ኢሜል info@africanchildforum.org

መቅድም

እንደሌሎች የአፍሪካ ሃገራት ሁሉ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ ህፃናትም ለተለያዩ ዓይነት ጥቃቶች፣ የመብት ጥሰቶች እና በደሎች ይጋለጣሉ። እነዚህ ሁኔታዎች አብዛኛውን ጊዜ የሚፈፀሙት ለህፃናቱ ተገቢውን ጥበቃና እንክብካቤ ያደርጋሉ ተብለው በሚታሰቡ ሰዎች እና ተቋማት መሆኑ ሁኔታውን እጅግ አሳሳቢ ያደርገዋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ፣

- ተጠቂ ህፃናት ሕጉን እና የፍትህ ሂደቱን ባለማወቅ ብሎም ክስን በፍርድ ቤቶች መከታተል የሚጠይቀውን ገንዘብ ለመሸፈን መቸገር፣

- ከሕግ ጉዳዩ ጎን ለጎን የሚነሱ እንደ የስነልቦና ምክር አገልግሎት፣ ህክምና እርዳታ እና ጊዜያዊ መጠለያ የመሳሰሉትን የማህበራዊ አገልግሎት ማግኘት አለመቻል፣

- የወንጀል ሕጉን የተላለፉ ሕፃናት በፍትህ ስርዐቱ ውስጥ ዕድሜያቸውን መሠረት ያደረገ አያያዝ አለማግኘት ፣ እና

- በሕግ፣ በፖሊሲና በአሰራር ላይ የሚታዩ ክፍተቶች ህፃናቱ ተገቢውን አገልግሎት እንዲያጡ እና ጥያቄዎቻቸው ምላሽ እንዳያገኙ አድርጓል።

የሕፃናት ሕጋዊ ከለላ ማዕከል በዚህ እትም ለቀረቡት ታሪኮች መነሻ የሆኑትን ጉዳዮችና ሌሎች የህፃናት መብቶች የሚመለከቱ ጉዳዮችን አስመልክቶ ነፃ የሕግ ምክርና የጥብቅና አገልግሎት በመስጠት፣ ከፍትህ አካላት ጋር በመወያየትና የመፍትሔ ሃሳቦችን በማመንጨት፣ ህብረተሰቡ ለሕፃናት ልዩ እንክብካቤ እንዲያደርግ ግንዛቤ በመፍጠር ቅስቀሳ በማድረግ ለብዙ ሕፃናት ብሩህ ተስፋ የሚሰጡ ሥራዎችን እየሰራ ይገኛል።

በዚህ የመጀመሪያ እትም ማዕከሉ ውጤት ያገኘባቸውን የስድስት ህፃናት ታሪኮች አካቷል። ህፃናቱ ባገኙት የሕግና የማህበራዊ አገልግሎቶች ከስጋት፣ ከበደልና ከጥቃት የተላቀቀ ሕይወት በመምራት ላይ ይገኛሉ። በዚህ ረገድ ማዕከሉ ያደረገው ጥረትና የተገኘው ውጤት ወላጆች፣ ህፃናት፣ ሕግ አውጪዎች ፣ የፍትህ አካላት እንዲሁም ሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎች እንዲያውቁት ማድረጉ ለወደፊት ለህፃናት የተጠናከረ ጥበቃን ይፈጥራል የሚል ፅኑ እምነት አለው። እያንዳንዱ መልካም እርምጃ ለህፃናት ሕይወት መለወጥና ከስጋትና ከጥቃት ነፃ ሆኖ ለመኖር የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። ስለዚህም ማዕከሉ አመርቂ የሕግ ውጤት ያስገኘባቸውን ጉዳዮች ተከታታይነት ባለው መልኩ እያሳተመ ለአንባቢያን ለማብቃት አቅዷል።

ማዕከሉ የባለታሪኮቹን የግል ሕይወትና ሚስጥር ለመጠበቅ ሲል «ከሕግ በላይ ማን አለ?» በሚለው ርዕስ ስር ከቀረበው ታሪክ በስተቀር በየታሪኮቹ ውስጥ የተጠቀሱት ስሞች በሙሉ የፈጠራ ስሞች መሆናቸውን ከወዲሁ ለመግለፅ ይወዳል።

የማዕከሉ መልዕክት

ህፃናት በት/ቤት፣ በቤትና በአከባቢያቸው የተለያዩ ዓይነት ጥቃቶች እና በደሎች ይፈፀምባቸዋል። በህፃናት ላይ ሊደርስ የሚችሉ ጥቃቶችን ለመከላከልና ተፈፅመው ሲገኙም ጥቃት አድራሾቹ ተገቢው የሕግ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ማድረግ የሁላችንንም ጥረትና ትብብር የሚጠይቅ ነው።

የሕፃናት ሕጋዊ ከለላ ማዕከል ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የበርካታ ህፃናትን መብቶች ለማስከበርና ለማስጠበቅ የተለያዩ ሥራዎችን እየሰራ ይገኛል። ማዕከሉ ቁጥራቸው በርካታ ለሆኑ ህፃናት ከጥቃት፣ ከበደል እና ከተለያዩ ችግሮች ተላቀው በሰላም እንዲኖሩ አድርጓል።

ማዕከሉ ከተመሰረተበት ከ1997 ዓ.ም. አጋማሽ እስከ 2001 ዓ.ም. ቁጥራቸው ከ 5000 በላይ ለሚሆኑ ህፃናት የሕግ እና የማህበራዊ ድጋፎችን ሰጥቷል። አገልግሎቱ የተሰጠውም ጥቃት ለደረሰባቸው እና መብታቸው ለተጣሰባቸው ህፃናት ብሎም የወንጀል ሕጉን ተላልፈው ለተገኙ ህፃናት ነው። በዚህ የመጀመሪያ እትም በማዕከሉና በተለያዩ አጋሮች ጥረት አመርቂ የሕግ እልባት ያገኙ የስድስት ሕፃናት ታሪኮችን እናካፍላችኋለን። ይህን ለማድረግ የተነሳንበት ምክንያትም በህፃናት የዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ ያሉትን ችግሮች ለማሳየት ፣ የህፃናትን መብት በማስከበር ሂደት ያሉ ክፍተቶችን ለመለየት ብሎም የተጠናከረ የሕግና የማህበራዊ ድጋፎች መኖር በህፃናት ህይወት ውስጥ የሚኖረውን ትልቅ ሚና በግልጽ ለማሳየት በማሰብ ነው።

የሕፃናት ሕጋዊ ከለላ ማዕከል ህፃናቱ ጉዳያቸው አስፈላጊውን የሕግ እልባት እንዲያገኝ እና ከየችግሮቻቸው እንዲላቀቁ የበኩላቸውን ጥረት ላደረጉ በሙሉ ከፍተኛ ምስጋና ያቀርባል። በተለይም የህፃናቱን ጉዳይ በሕግ ለመከታተል እንዲቻል ብሎም አስፈላጊውን የማህበራዊና የስነልቦና አገልግሎት ለመስጠት የገንዘብ ድጋፍ ላደረጉልን ለፕላን ኢንተርናሽናል እና ለሕፃናት አድን ድርጅቶች ህብረት (ዴንማርክ፣ ስዊድን፣ ኖርዌይ እና ፊንላንድ) ምስጋናውን ያቀርባል።

በመጨረሻም ማዕከሉ የህፃናቱ ጉዳይ የሕግ መፍትሄ ያገኝ ዘንድ ለማዕከላችን ሪፖርት ላደረጉ፣ እውነትን መሠረት አድርገው ሕግ ፊት ቀርበው ለመስከሩ፣ ህፃናቱን ከጥቃት ለመታደግ የሙያ ግዴታቸውን ላበረከቱ የፍትህ አካላት፣ በተለይም ያለምንም የሙያ ክፍያ የህፃናቱ ጥቃት ተሰምቷቸው ለውጤት ለተጉ የማዕከሉ ጠበቆች ከፍ ያለ ምስጋናውን ያቀርባል።

ሄለን ሰይፉ
በአፍሪካ ሕፃናት ፖሊሲ መድረክ
የሕፃናት ሕጋዊ ከለላ ማዕከል
ዳይሬክተር

ማውጫ

መቅድም i

የማዕከሉ መልዕክት ii

ማውጫ iii

ስኬታማ ጉዳዮች

ሀ) በዘመዳሞች መካከል የተደረገ የፍ/ቤት ክርክር 1

(ሞግዚትነት)

ለ) የአፍ ዘመድ 3

(የይዞታ መብት እና ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ መውጣት)

ሐ) ከሕግ በላይ ማን አለ? 5

(በህፃን ላይ የተፈፀመ የነፍስ ግድያ ወንጀል)

መ) ለስሙ - አባት 6

(አባት በልጁ ላይ ስለፈፀመው የአስገድዶ መድፈር ወንጀል)

ሠ) በ12 ዓመቱ የ16 ዓመት እስራት 8

(በወንጀል ጉዳይ ገብተው የተገኙ ህፃናት የፍትህ አስተዳደር)

ረ) በዲ.ኤን.ኤ. አባትነት ሲረጋገጥ 9

(አባትነትን በፍ/ቤት ውሳኔ ማረጋገጥ)

የሕፃናት ሕጋዊ ከለላ ማዕከል ጥሪ 10

በዘመዳሞች መካከል የተደረገ የፍ/ቤት ክርክር
(ሞግዚትነት)

ሳሙኤል በአሁኑ ጊዜ የ15 ዓመት ህፃን ሲሆን የተወለደውም ከጋብቻ ውጪ በተፈፀመ የግብረስጋ ግንኙነት ነው። ሳሙኤል 1 ዓመት ሲሞላው ወላጅ እናቱ ልጇን ለማሳደግ አቅም ስላልነበራትና አባቱ ታደለም ይህን ኃላፊነት ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆኑ ሳሙኤል ለአያቱ ተሰጠ። ነገር ግን አያቱ በጤና መታወክ ምክንያት ሳሙኤልን ማሳደግ ባለመቻላቸው አክስቱ ሂሩት ሳሙኤልን የማሳደግ ሃላፊነትን ተረከበች። አባቱ ታደለም በቂ የሆነ መተዳደሪያ እና ስራ የነበረው ቢሆንም ሂሩትን ለመደጎም ምንም ዓይነት ጥረት ባለማድረጉ ህፃኑን ተንከባክቦ ማሳደግ ሙሉ ለሙሉ የሂሩት ኃላፊነት ሆነ።

ሳሙኤል 13 ኛ ዓመቱን እንዳከበረ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትኖር የነበረችው ወላጅ እናቱ ከጊዜ በኃላ ያፈራችውን በርካታ ሀብት እና ንብረት ትታ ሞተች። ወላጅ አባቱም ወዲያውኑ ለሳሙኤል ሞግዚት ሆኜ ልሾም የሚል ጥያቄ ይዞ ወደክልሉ ወረዳ ፍ/ቤት ቀረበ። ፍ/ቤቱም አባትነቱን አረጋግጦ በጠየቀው መሠረት የሳሙኤል ሞግዚት እና አሳዳሪ አድርጎ ሾመው። ታደለም የፍ/ቤቱን ውሳኔ በእጁ እንዳስገባ በሚች ስም በባንክ ተቀምጦ የነበረውን እና የሳሙኤል የውርስ ድርሻ የሆነውን ከ30000 (ሠላሳ ሺህ) ብር በላይ የሆነ ገንዘብ አውጥቶ ለራሱ ጥቅም አዋለው። ይህ አልበቃ ብሎት የሳሙኤል የውርስ ድርሻ የሆነውን ተንቀሳቃሽ እና የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመሸጥ ሲያስማማ ሂሩት ትሰማና ታደለ የሳሙኤል ሞግዚት እንዲሆን ውሳኔ ላስተላለፈው ፍ/ቤት የመቃወሚያ አቤቱታ አቀረበች። በመቃወሚያ ማመልከቻዋም ለሳሙኤል ሞግዚት ሆኖ የተሾመው አባት የፈፀመውን የእምነት ማጉደል ድርጊት ገልፃ፣ ሳሙኤልን ከህፃንነቱ ጀምሮ ያለማንም ድጋፍ እና እርዳታ ተንከባክባ ያሳደገችው እሷ ብቻ መሆኗን ለፍ/ቤቱ አሳውቃ፣ ፍ/ቤቱ ወላጅ አባትየውን የሳሙኤል ሞግዚት አድርጎ የሾመበትን ውሳኔ ሽሮ በምትኩ እርሷን ሞግዚት አድርጎ እንዲሾማት ጥያቄ አቀረበች።

በክርክራቸው ወቅት የህፃኑ ሞግዚት ማን መሆን እንዳለበት ለመወሰን ያስችላል ተብሎ የተመሠረተው ጭብጥ ከሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች **ለህፃኑ ማን የቀረበ ዝምድና አለው?** የሚል እንጂ **የትኛው ወገን የህፃኑን ጥቅምና ደህንነት በይበልጥ ያስጠብቃል?** የሚል ባለመሆኑ ፍ/ቤቱ የሂሩትን ክርክር በአግባቡ ሳያስተናግደው ይቀራል። እንዲያውም ሳሙኤል ልጇ ስላልሆነ ይህ ጉዳይ እሷን እንደማይመለከታት በተደጋጋሚ በችሎት ይነገራት ነበር። በመጨረሻም ፍ/ቤቱ የሂሩትን አቤቱታ ውድቅ አድርጎ መዝገቡን ዘጋ።

ሂሩት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመቃወምና ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በሚል ጉዳዩን በይግባኝ በመቀጠልም በሠበር[1] ለክልሉ ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍ/ቤቶች በየተራ አቀረበች። ነገር ግን አቤቱታዎቿ **«የህፃኑ አባት በህይወት እያለ ለህፃኑ ሞግዚት መሆን አትችይም»** በሚል ምክንያት ውድቅ ሆኑባት። ሂሩት ከስር እስከ ላይ በተዋቀሩት የክልል ፍ/ቤቶች ለአቤቱታዋ መፍትሔ የሚሰጣት ባታገኝም በአገር አቀፍ ደረጃ የቀራትን አንድ የመጨረሻ እድል መሞከር ስለነበረባት ጉዳዩን ወደ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት አቀረበች።

ሂሩት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት ባቀረበችው አቤቱታ የክልል ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ሲሰጡ ሊያጣሩ ይገባቸው የነበረው ጭብጥ **«ለህፃኑ ማን የቀረበ ዝምድና አለው?»** የሚለውን ሳይሆን **«የህፃኑን ጥቅምና ደህንነት የሚያስጠብቀው የትኛው**

[1] ሠበር ሰሚ ችሎት ማለት የስር ፍ/ቤቶች ባስተላለፉት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ሲኖር የመጨረሻው አቤቱታ የሚቀርብበት በጠቅላይ ፍ/ቤት ስር የሚገኝ ችሎት ነው።

ወገን ነው?» የሚለውን ሊሆን እንደሚገባ ገልፃ ተከራክረች፡፡ ይህም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ-መንግስት አንቀፅ 36/2/ እና በዓለም አቀፍ የህፃናት መብቶች ስምምነት አንቀፅ 3/1/ ስር **በህፃን ጉዳይ ላይ ውሳኔ የሚያስተላልፉ አካላት ሁሉ ለህፃኑ ጥቅምና ደህንነት መከበር ቅድሚያ መስጠት እንደሚገባቸው** የተደነገገውን መርህ መሠረት ያደረገ አቤቱታ ነበር፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሠበር ሰሚ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎቻቸውን መርምሮ፣ በተለይም የአባትየውን እምነት ማጉደል በተመለከተ የቀረበውን አቤቱታ ተመልክቶና በጉዳዩ ላይ ሳሙኤል ያለውን አስተያየት አድምጦ ሂሩት ባቀረበችው አቤቱታ መሠረት የክልል ፍ/ቤቶች በየደረጃው የሰጡትን ውሳኔ በመሻር ሂሩት የሳሙኤል ሞግዚት እንድትሆን ውሳኔ አስተላለፈ፡፡ በፍርድ ሀተታውም የዓለም አቀፍን የህፃናት መብቶች ስምምነት አንቀፅ 3/1/ን ጠቅሶ ዝርዝር ሕጎች ይህን መሠረታዊ መርህ ተንተርሰው መተርጎም እንዳለባቸው በማስፈር በሥር ፍ/ቤቶች ተመሳሳይ ጉዳይ ሲያጋጥም ተፈፃሚ የሚሆን ፈር ቀዳጅ ውሣኔ ሰጠ፡፡

በአሁኑ ጊዜም ሂሩት በተሠጣት የሞግዚትነት ስልጣን ታደለን ጨምሮ የሳሙኤልን የውርስ ድርሻ ያለአግባብ ይዘው እየተጠቀሙበት ካሉ ግለሰቦች ላይ ለማስመለስ ፋይል ከፍታ በክርክር ላይ ትገኛለች፡፡

ማዕከሉም ሂሩት ለክልሉ ወረዳ ፍ/ቤት መቃወሚያ ካቀረበችበት ጊዜ ጀምሮ በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በነበራት ክርክር ብሎም የሳሙኤልን የውርስ ሃብት ለማስመለስ በምታደረገው ጥረት የሕግ ምክር፣ የተለያዩ ማመልከቻዎችን የማዘጋጀት እና የጥብቅና አገልግሎቶችን ሰጥቷታል፡፡

መንግስታዊም ሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣ ፍርድ ቤቶች እና የአስተዳደር ባለስልጣናት የህፃናትን ጉዳይ በሚመለከቱበት ጊዜ የህፃናቱን ጥቅም እና ደህንነት በቀዳምትነት ማየት እንዳለባቸው በሕገመንግስቱ አንቀፅ 36/2፣ በአለም አቀፉ የህፃናት መብቶች ስምምነት አንቀፅ 3፣ በአፍሪካ የህፃናት መብቶች እና ደህንነት ቻርተር አንቀፅ 4 እና በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀፅ 218 ላይ ተደንግጓል፡፡

የአፍ ዘመድ
(በይዞታ መብት እና ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ መውጣት)

ሳምራዊት እና ሳምሶን እህትና ወንድም ናቸው። ሳምራዊት 15 ዓመቷ ሲሆን ወንድሟ ሳምሶን ደግሞ 10 ዓመቱ ነው። ሁለቱንም ወላጆቻቸውን በሞት አጥተዋል። ሳምራዊት ቀን እየተማረች በትርፍ ጊዜዋ መኪና በመጠበቅ አነስተኛ ገቢ ታገኛለች። ወንድሟ ደግሞ ከአንድ በጎ አድራጊ ድርጅት በሚደረግለት መጠነኛ የገንዘብ ድጋፍ እየታገዘ ይማራል። ሁለቱም የሚኖሩት ወላጆቻቸው ይኖሩበት በነበረው የቀበሌ ቤት ውስጥ ነው። በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉ በክፍለ ሃገር የምትኖር አክስታቸው «ያግዛችኋል ፣ ያስተዳድራችኋል» ብላ ባለቤቷን ወደ እነርሱ ላከች።

ሊያስተዳድራቸው የመጣው የአክስታቸው ባል ግን ሸክማቸውን የሚጨምር እንጂ የሚያቀል አልሆነላቸውም። ወላጆቻቸውን አጥተው ኑሮን በግላቸው መጋፈጣቸው ያላነሳቸው እነዚህ ሕፃናት ያለቻቸውንም ቁራሽ ከ «አስተዳዳሪያቸው» ጋር መካፈል የግድ ሆነባቸው። እሱም ሳያንስ ከመኪና ጥበቃ ሥራም ሆነ ከበጎ አድራጊው ድርጅት የሚገኘውን ገንዘብ በሙሉ ለእርሱ እንዲሰጡት ከማስገደዱም ሌላ ሳምራዊት ላይ የወሲብ ጥቃት ለመፈፀም ተደጋጋሚ ሙከራ ማድረግ ጀመረ። ሳምራዊት ሁኔታው ከአቅሟ በላይ ሲሆንባት ቤቷን ለቃ በየጎረቤቱ እና በየጓደኞቿ ቤት ማደር ጀመረች። ወንድሟም እርሷ በሌለችበት መኖር ስለከበደው ሲቻለው በጓደኞቹ ቤት፣ አሊያም በጎዳና ማደር ጀመረ።

የእነሳምራዊት ከቤት መውጣት ያልቆረቆረው የአክስታቸው ባል ህፃናቱ የትና እንዴት እንደሚኖሩ ለማወቅ ግድ ሳይኖረው ባለቤቱንና ልጁን አምጥቶ የህፃናቱን ቤት መኖሪያው በማድረግ ተቀመጠ። ከጅምሩም አመጣጡ የማረፊያና የቀለብ ወጪ ሳይኖርበት ለራሱ በከተማ ሥራ ለማፈላለግ፣ ብሎም የቤተሰቡን ከክፍለሃገር ወደ አዲስ አበባ መምጣት ለማመቻቸት እንጂ የሙት ልጆችን ለመንከባከብ እንዳልሆነ እያደር ግልጽ ሆነ።

ሳምራዊት ለችግሩ መፍትሔ ፍልጋ መጀመሪያ ያመራችው ወደምትኖርበት ቀበሌ የሴቶች ጉዳይ ፅ/ቤት ነበር። ጉዳዩ የሚመለከታቸው የቀበሌው ባለሞያዎች የአክስትየውን ባል ጠርተው አነጋገሩት። ሆኖም ግለሰቡ ፈፅመ የተባለውን ከመካዱ በተጨማሪ «ቤቱ የባለቤቱ እናት ቤት ስለሆነ ባለቤቱ የወራሽነት መብት አላት፤ ስለዚህም ቤቱን አልቅም» በሚል አሻፈረኝ አለ። «ሳይደግስ አይጣላም» እንዲሉ ከቀበሌው የሴቶች ጉዳይ ቢሮ ሠራተኞች አንዱ የሕፃናት ሕጋዊ ከለላ ማዕከል ስለሚሰጣቸው የሕግ አገልግሎቶች ሰምቶ ስለነበር ነገሩ ከቀበሌው አቅም በላይ መሆኑን ሲረዳ ሳምራዊትን ወደ ማዕከሉ ይዟት መጣ።

ማዕከሉም ለሳምራዊት የምክር አገልግሎት በሚሰጥበት ወቅት የሚኖሩበት ቤት የቀበሌ ቤት መሆኑን፣ አያታቸው ከመሞታቸው በፊትም ሆኑ በኋላ እርሷና ወንድሟ ከእናታቸው ጋር ሆነው ይኖሩበት እንደነበር፣ አሁን የመጣችው አክስታቸው ግን ከእናታቸውም ሆነ ከአያታቸው ሞት በፊት ከቀበሌው መልቀቂያ ወስዳ ከአዲስ አበባ ውጪ ትዳር መስርታ እና ወልዳ ትኖር እንደነበር ተገነዘበ።

ሳምራዊት ህፃን በመሆኗ ክስ አቅርባ የእሷን እና የወንድሟን መብት ለማስጠበቅ በሕግ ችሎታ ስለሌላት እነሱን በሞግዚትነት ወክሎ ክስ ለመመስረት ፈቃደኛ የሆነ ዘመድ ስለመኖሩም

ስትጠየቅ ቤታቸውንና ንብረታቸውን ተቆጣጥረው ከሚገኙት አክስቷ እና የአክስቷ ባል ውጪ ምንም ዘመድ እንደሌላቸው ገለፀች። በዚህም ምክንያት ሳምራዊት 14 ዓመት ስለሞላት መብታቸውን ለማስጠበቅ በሕጉ መሰረት ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ እንድትወጣ ማድረግ ብቸኛ አማራጭ እንደሆነ ማዕከሉ አመነበት። ከዚህ በኋላ ማዕከሉ እነሳምራዊት የሚኙ እናታቸው ወራሾች መሆናቸው እንዲረጋገጥ፣ ሳምራዊት ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ እንድትወጣ እንዲሁም ለታናሽ ወንድሟ ሞግዚት የመሆን ሥልጣን እንድታገኝ ለፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርቦ ይኸው ተወሰነለት።

በመቀጠልም የፍርድ ቤቱን ውሳኔ በመያዝ ህፃናቱ በቀበሌው ቤት በነዋሪነት ተመዝግበው የሚገኙ በመሆናቸው የቤቱ ይዞታ በሳምራዊት ስም እንዲዞርና የኪራዩ ውልም በስሟ እንዲፈረም ተጠየቀ። ቀበሌወም በዚሁ መሰረት ፈፀመ።

ቀጣዩ ሥራ ከነጓዛቸው መጥተው በሕፃናቱ ቤት የተደላደሉትን «ዘመዶች» ከቤት ማስወጣት ነበር። በዚሁ መሰረትም ማዕከሉ ጉዳዩን በስምምነት ለመጨረስ በማሰብ የህፃናቱን «አክስት» እና ባሏን ቢጠራም በጥሪው መሰረት የመጣችው አክስታቸው ብቻ ነበረች። ከእርሷ ጋር በነበረው ውይይትም የቀበሌ ቤት በውርስ ሊተላለፍ እንደማይችል፣ በቤቱ ቀጣይ መብት የሚኖራቸው ዋናዎቹ ተከራዮች በሕይወት በነበሩበት ወቅት አብረዋቸው በጥገኝነት ይኖሩ የነበሩ ሰዎች እንደሆኑ፣ እርሷ ግን ከእናቷም ሆነ ከእህቷ ሞት በፊት መልቀቂያ ወስዳ በመሄዷ በቤቱ ላይ ምንም ዓይነት የይገባኛል ጥያቄ ለማቅረብ እንደማትችል ተነገራት። የህፃናቱ አክስት እንደመሆኗም ደህንነታቻውን መጠበቅ የእሷም ግዴታ ሊሆን እንደሚገባ ሲነገራት እና ስትወቀስ «የትዳር ጉዳይ» ሆኖባት እንጂ ነገሩ እርሷንም እንደተሰማት ገልጻ ቤት ለማፈላለግ የ15 ቀን ጊዜ ገደብ እንዲሰጣትና ነገሩንም ባለቤቷም እንዲያውቀው የ«ልቀቁ» ማስጠንቀቂያ በሁለቱም ስም እንዲፃፍላት ጠየቀች።

የማስጠንቀቂያ ደብዳቤውም ተፃፈ፤ የተባለው 15 ቀንም አለፈ። ሰዎቹ ግን አሁንም ቤቱን አልለቀቁም። እንዲያውም «ብትፈልጉ ክሰሱን» በማለታቸው ቤቱን ለማስለቀቅ ማዕከሉ በባልና ሚስቱ ላይ ክስ መስርቶ አስወሰነ። ያም ሆኖ ባለመልቀቃቸው በአፈጻጸም ተገደው ቤቱን ለህፃናቱ እንዲያስረክቡ አደረገ። ከዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ በኋላ እነሳምራዊት ቤታቸውን ተረክበው በነፃነትና በሰላም ኑሯቸውን ጀመሩ።

በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀፅ 312 እና 313 መሰረት ዕድሜው 14 አመት የሆነው ህፃን ለራሱ ጥቅም ሲባል ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ሊወጣ እንደሚችል እና እንደ አዋቂ ሊቆጠር ብሎም የሕግ ችሎታ ሊያገኝ እንደሚችል ተደንግጓል።

ከሕግ በላይ ማን አለ?
(በህፃን ላይ የተፈፀመ የነፍስ ግድያ ወንጀል)

ኤፍሬም የ16 ዓመት ህፃን ነበር። በተንቀሳቃሽ ስልክ ስርቆት በመጠርጠሩ ታስሮ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ተወሰደ። በጣቢያ ቆይታውም ሁለት የፖሊስ አባሎች ከተጠረጠረበት የወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ በተጠቀሙት ሕገወጥ የምርመራ አካሄድ ከባድ ድብደባ ደረሰበት። ድብደባውም አፍሬምን ቋሚ ለሆነ የአካል ጉዳት በመዳረጉ የአልጋ ቁራኛ ሆኖ ነበር።

የኤፍሬም ቤተሰቦች የሕግ ድጋፍ እና የህክምና አገልግሎት ለማግኘት ወደ ሕፃናት ሕጋዊ ከለላ ማዕከል የመጡት አስከፊው ድብደባ ከተፈፀመ ከአራት ወራት በኋላ ነበር። ማዕከሉም ወዲያውኑ የወንጀሉን ጉዳይ ለአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን በማሳወቅ በሁለቱ የፖሊስ አባላት ላይ ምርመራ እንዲጀመር አደረገ። በምርመራው ሂደትም ኤፍሬም የምስክርነት ቃሉን እንዲሰጥ በማድረግ ተጠርጣሪዎቹ የፖሊስ አባላት በቁጥጥር ስር እንዲውሉና ክስ እንዲመሰረትባቸው አስችሏል። ከዚህ በተጨማሪ አንፑካን (አሶሴሽን ፎር ኔሽን ዋይድ አክሽን ፎር ዘ ፕሪቨንሽን ኦፍ ኤንድ ፕሮቴክሽን አጌንስት ቻይልድ አቢውዝ ኤንድ ኔግሌክት) ከተባለው መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ጋር በመተባበር ኤፍሬም በጥቁር አንበሳ፣ የካቲት 12 እና ቤቴል ሆስፒታሎች የህክምና እርዳታ እንዲያገኝ ጥረት ተደርጎ ነበር። ሆኖም ድብደባው ከባድ የአካል ጉዳት ያደረሰበት በመሆኑ ከ 6 ወራት ስቃይ በኋላ ህይወቱ አለፈ።

ከኤፍሬም ሞት በኃላም ዐቃቤ ሕግ በሁለቱ የፖሊስ አባላት ላይ በነፍስ ግድያ ወንጀል ክስ መሰረተ። በመቀጠልም ክሱን ሲመለከት የነበረው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሦስተኛ ወንጀል ችሎት **ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም.** በዋለው ችሎት ሁለቱንም የፖሊስ አባላት በሰው መግደል ወንጀል ጥፋተኛ ሆነው በማግኘቱ እያንዳንዳቸው **በ 7 ዓመት ፅኑ እስራት** እንዲቀጡ ወሰነ። ሆኖም ለዚህ አይነት አሠቃቂ የወንጀል ድርጊት 7 ዓመት የእስራት ቅጣት ተመጣጣኝ ባለመሆኑ ዐቃቤ ሕግ ይግባኝ እንዲጠይቅ ማዕከሉ አሳስቧል። ዐቃቤ ሕግ ባቀረበው ይግባኝ መሠረትም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፖሊስ አባላቱ ላይ በስር ፍርድ ቤት የተጣለው ቅጣት ከተፈፀመው ወንጀል ጋር ተመጣጣኝ ሆኖ ባለማግኘቱ የቅጣት መጠኑን ወደ **10 ዓመት ፅኑ እስራት** ከፍ አድርጎታል።

የወንጀሉ ጉዳይ እልባት ካገኘ በኋላም የኤፍሬም ቤተሰቦች በልጃቸው ሞት ምክንያት ለደረሰባቸው ጉዳት በፍትሐብሔር ካሳ እንዲያገኙ ማዕከሉ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል።

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገመንግስት አንቀፅ 12/2 መሠረት ማንኛውም ለሕዝብ አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋመ መ/ቤት ሰራተኛ እና ኃላፊ ኃላፊነቱን አጓድሎ ሲገኝ ተጠያቂ ይሆናል።

ለስሙ አባት
(አባት በልጁ ላይ የፈፀመው የአስገድዶ መድፈር ወንጀል)

ገና የ7 ዓመት ህፃን እያለች አባትና እናቷ የተለያዩት ሰብለ በአሁኑ ጊዜ የ13 ዓመቷ ነው። ወላጆቿ ከተለያዩ በኋላ ሰብለ የምትኖረው ከአባቷ ከሞገስ ጋር ነበር። ሞገስ የሰብለ እናት ከቤት ከወጣችበት ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ ሴቶችን እያገባ ይፈታ ነበር። ከሁለት ዓመት በፊት ሞገስ የመጨረሻ ሚስቱ ጥላው እንደሄደች ሰብለን ሊደፍራት ሲሞክር የሰብለን ጩኸት የሰሙ ጎረቤቶች በር ገንጥለው በመግባት አስጣሏት። ሆኖም ወንጀሉ ወዲያውኑ ለፖሊስ ሪፖርት ሳይደረግ ቀረ።

በዚህ መካከል ሞገስ ሰብለን ከመኖሪያ አካባቢያቸው በማራቅ በአያቷ ቤት እንድትቀመጥ አደረገ። የሰብለ አያትም ህፃኗን ለመያዝ ፈቃደኛ ስላልነበሩ ከቤታቸው አስወጧት። ሰብለ ተመልሳ ወደ አባቷ ቤት ብትሄድም አባቷ ድርጊቱን ከፈፀመባት ቀን ጀምሮ በአካባቢው ታይቶ እንደማይታወቅ ጎረቤቶች ነገሯት።

መዜጃ ያጣችው ሰብለ መንገድ ዳር ተቀምጣ ስታለቅስ የሰፈሯ ሰው የሆኑት ወ/ሮ አለሚቱ ተመልክተዋት ምን ሆና እንደምታለቅስ ሲጠይቋት አባቷ ያደረሰባትን አሰቃቂ በደል ነገረቻቸው። ወ/ሮ አለሚቱ ታሪኯን ሰምተው ጥለዋት መዜድ ስለከበዳቸው ወደ ቤታቸው ወሰዷት። የወ/ሮ አለሚቱ ልጅም የሕፃናት ሕጋዊ ከለላ ማዕከል ስለሚሰጣቸው የሕግ አገልግሎቶች ታውቅ ስለነበር ሰብለን ወደ ማዕከሉ ይዛት መጣች።

ማዕከሉም ስለጉዳዩ ከህፃኗ አንደበት ከሰማ በኋላ በቅድሚያ የሕክምና አገልግሎት ታገኝ ዘንድ ሰብለን ወደ ጋንዲ ሆስፒታል ወሰዳት። የህክምናው ውጤት እንደተገኘ ፖሊስ የወንጀል ምርመራ እንዲያጣራ ተጠየቀ። በዚሁ መሠረትም ምርመራው የህፃኗን እና የዐይን ምስክሮችን ቃል በመቀበል ተጀመረ። ይሁንና ጉዳዩን የያዘው መርማሪ ፖሊስ በህክምና ማስረጃው ላይ «የክብረ ንፅህና መገሰስ የለም» የሚለውን የባለሞያ አስተያየት ሲመለከት ህፃኗ ክሱን እንድትተው የመከራት ቢሆንም ማዕከሉ የክብረ ንፅህና መገሰስ ባይኖርም የመድፈር ሙከራ መደረጉ በራሱ ወንጀል መሆኑን በመግለፅ አጥብቆ በመከራከሩ ክሱ እንዲቀጥል ቢደረግም ሞገስ በመሰወሩ ምክንያት ምርመራው ሳይቋጭ ቀረ።

ማዕከሉም ፖሊስ ተጠርጣሪውን ለመያዝ ከፍ/ቤት የመያዣ ትዕዛዝ ማውጣት ብቻ ሳይሆን ተጠርጣሪው ይገኝበታል ተብሎ በሚጠረጠርባቸው ቦታዎች ተገቢውን ክትትል ማድረግ እንዳለበት ደጋግሞ አመለከተ። ነገር ግን በፖሊስ በኩል ተገቢው ጥረት ባለመደረጉ ሞገስን ሕግ ፊት ማቅረብ ሳይቻል ቀረ። የተፈጠረውን ክፍተት ለመሙላት ስለተጠርጣሪው አግባብነት ያለውን መረጃ የሚያሰባስብና ከፖሊስ ጋር በመተባበር የሞገስን በቁጥጥር ስር መዋል እውን ለማድረግ የሚያግዝ በጎ ፈቃደኛ ማዕከሉ መደበ። ከ1 ዓመት ትዕግስት አስጨራሽ ክትትል በኋላም ሞገስ በፖሊስ ቁጥጥር ስር ዋለ።

ፖሊስም የተጠርጣሪውን ቃል በመቀበል ተቋርጦ የነበረውን የወንጀል ምርመራ ካጠናቀቀ በኋላ መዝገቡን ወደ ዐቃቤ ሕግ ፅ/ቤት ላከ። ዐቃቤ ሕግም የተሻሻለውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 27፣ 627 እና 654(ጀ) ጠቅሶ በአስገድዶ መድፈር ሙከራና በዘመዳሞች መካከል የግብረስጋ ግንኙነት

መፈፀም ሙከራ ወንጀል በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክስ መሠረተ፡፡ ሞገስ የተከሰሰባቸውን የወንጀል ድርጊቶች ሙሉ በሙሉ ቢክድም ጉዳዩን ሲመለከት የነበረው ፍ/ቤት የህግኗን ምስክርነት፣ የዐይን ምስክሮችን ቃልና የህክምና ማስረጃውን መርምሮ **ግንቦት 4 ቀን 2000 ዓ.ም.** በዋለው ችሎት በተከሳሹ ላይ **የጥፋተኝነት ውሳኔ** አስተላለፈ፡፡ በመቀጠልም **ሰኔ 5 ቀን 2000 ዓ.ም.** በዋለው ችሎት ተከሳሹ **በ18 ዓመት ፅኑ እስራት** እንዲቀጣ ተወሰነ፡፡

ሰብለ ወደማዕከላችን ከመጣችበት ጊዜ ጀምሮ የሕግ ጉዳዩ እልባት እስከሚያገኝ ድረስ በጊዜያዊ መጠለያ የቆየች ሲሆን፣ የእናቷን እውነተኛ ማንነትና ትክክለኛ አድራሻ ለማግኘት ባለመቻሉ ምክንያት ማዕከሉ በአሁኑ ወቅት በህፃናት ማሳደጊያ ውስጥ ገብታ በቋሚነት እንድትኖር አድርጓል፡፡

በተሻሻለው የወንጀል ሕግ፡-

አንቀፅ 27(1) እና (3) መሠረት ወንጀልን ለመፈጸም ሙከራ ማድረግ በራሱ ለወንጀል ድርጊቱ በተቀመጠው የቅጣት መደብ እንደሚያስቀጣ ተደንግጓል፡፡

አንቀፅ 627 መሠረት ዕድሜዋ ከ13 ዓመት በታች በሆነች ህፃን ላይ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል መፈፀም ከ15 ዓመት እስከ 25 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ያስቀጣል፡፡

በአንቀፅ 654 መሠረት በዘመዳሞች መካከል ታስቦ የሚፈፀም የግብረስጋ ግንኙነት ከሦስት አመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ያስቀጣል፡፡

በ 12 ዓመቱ የ16 ዓመት እስራት

(በወንጀል ጉዳይ ገብተው የተገኙ ህፃናት የፍትህ አስተዳደር)

ቶሎሳ የ12 ዓመት ህፃን ሲሆን በኦሮሚያ ክልል በሚገኝ ወረዳ ፍ/ቤት በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘቱ የ16 ዓመት እስራት ተፈረደበት፡፡ በዚህም ምክንያት በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኘው የወጣት ጥፋተኞች ማረሚያ ተቋም እንዲገባ ተደረገ፡፡ ስለአስተዳደጉ ሲናገር እናቱ አረቄ እያወጣች ቤተሰቡን እንደምታስተዳድርና አባቱም በየቀኑ «መጠጥ ጠጥተህል» በሚል ሰበብ እንደሚደበድበው ይገልፃል፡፡ ቶሎሣ ከፍ/ቤቱ ውሳኔው በኋላ አባቱ ይግባኝ እንዲጠይቁለት ቢማፀንም አባትየው ፈቃደኛ አልሆኑም፡፡ ወደ ማረሚያ ተቋም ከተዛወረ በኋላም እናቱም ሆኑ አባቱ አንድም ቀን ብቅ ብለው ሳያዩት የማረሚያ ቤት ኑሮውን መግፋት ጀመረ፡፡

ማዕከሉ ጉዳዩን እንደሰማ ውሳኔው በወንጀል ሕጉ መሰረት ዕድሜው ከ9 - 15 ዓመት በሆነው አንድ ህፃን ላይ ሊወሰን ከሚችለው የቅጣት ጣራ በላይ በመሆኑ የሕግ ስህተቱን ለማስተካከል ጥረት ማድረግ ጀመረ፡፡ የፍርድ ውሳኔው ከተሰጠ ከ2 ወር በላይ ስለሆነው በጉዳዩ ላይ ይግባኝ መጠየቅ ባይቻልም የወንጀል ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ውሳኔውን ላስተላለፈው ፍ/ቤት አቤቱታ ቀረበ፡፡

ፍርድ ቤቱም በ12 ዓመቱ ሕፃን ላይ የተላለፈው የ16 ዓመት እስራት ሕጉ ከሚፈቅደው በላይ መሆኑን በመቀበል እስራቱን ወደ 5 ዓመት ዝቅ አደረገው፡፡ ቶሎሳ በማረሚያ ቤት ቆይታው ገንቢ የባሕሪ ለውጥ ከታየበት አምስቱን ዓመት ሳይጠብቅ በአመክሮ ለመለቀቅ እንደሚችል በውሳኔው ላይ ተጠቅሷል፡፡ ማረሚያ ተቋሙም በልጁ ላይ የሚታየውን የባህሪ መሻሻል በተመለከተ በየጊዜው ለፍርድ ቤቱ ሪፖርት እንዲያቀርብ ታዟል፡፡

በዓለም አቀፍ የሕፃናት መብቶች ስምምነት መሠረት በወንጀል ጉዳይ ገብተው የተገኙ ህፃናትን ለማረም እስራት የመጨረሻው አማራጭ ሊሆን እንደሚገባ የተደነገገ ሲሆን በሀገራችን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 168/2 መሠረትም በወንጀል ጉዳይ ገብተው በተገኙ እና ዕድሜያቸው ከ9 - 15 ዓመት በሆኑ ሕፃናት ላይ ሊተላለፍ የሚችለው ከፍተኛ የእስራት ቅጣት መጠን 10 ዓመት ነው፡፡

በዲ.ኤን.ኤ. አባትነት ሲረጋገጥ
(አባትነትን በፍ/ቤት ውሳኔ ማረጋገጥ)

ለማ ከጋብቻ ውጭ በተፈፀመ የግብረስጋ ግንኙነት የተወለደ ሲሆን በአሁኑ ወቅት የ10 ዓመት ህፃን ነው። ለማ በተፀነሰበት ወቅትም ሆነ ከተወለደ በኋላ አባቱ ወርቁ ልጅነቱን ለመቀበል ፍቃደኛ አልነበረም። የለማ እናት አዜብም ምንም ዓይነት ገቢ የሌላት በመሆኑ ልጇን ለማሳደግ አልቻለችም። በዚህም ምክንያት ለማን ገጠር ለሚኖሩ ወላጆቿ ለመስጠት ተገደደች።

ሆኖም የለማ አያት በሞት በመለየታቸው ምክንያት ለማን የማሳደጉ ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ አዜብ ላይ ወደቀ። አዜብም የቀን ስራም ሆነ የተገኘውን ማንኛውንም ስራ በመሰራት ልጇን ለማሳደግ ስትጥር ቆየች። በኋላም ለማን ብቻዋን ማሳደጉ ከአቅሟ በላይ ሲሆንባት ወርቁ የአባትነት ኃላፊነቱን እንዲወጣ ለማድረግ የሕግ እርዳታ ፍለጋ ወደ ሕፃናት ሕጋዊ ከለላ ማዕከል ቀረበች።

ማዕከሉም ወርቁን በመጥራት ጉዳዩን በስምምነት ለመጨረስ ቢሞክርም ወርቁ ግን ቀርቦ ለመነጋገር ፍቃደኛ ባለመሆኑ ማዕከሉ አባትነት እንዲረጋገጥ ለፍርድ ቤት የሚቀርብ አቤቱታ አዘጋጅቶ ለአዜብ ሰጣት። ነገር ግን አዜብ የወርቁን አባትነት ለማረጋገጥ ምንም ዓይነት የሰውም ሆነ የፅሁፍ ማስረጃ የሌላት በመሆኑ ለፍርድ ቤት በቀረበው አቤቱታ የወርቁን አባትነት ለማረጋገጥ የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ እንዲደረግ ፍ/ቤቱ እንዲያዝ ተጠየቀ።

በፍርድ ቤቶች አሰራር ባልተለመደ ሁኔታ የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ እንዲደረግ ትዕዛዝ ተሰጠ። ማዕከሉም አስፈላጊውን ወጪ ከመሸፈን ጀምሮ የዲ.ኤን.ኤ ምርመራው በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት እንዲፈፀም ድጋፍ ሲያደርግ ቆየ። በመጨረሻም የምርመራው ውጤት ወርቁ የለማ አባት መሆኑን አረጋገጠ። ፍርድ ቤቱም ውጤቱን መሠረት በማድረግ የወርቁን አባትነት የሚያረጋግጥ ውሳኔ አስተላለፈ።

አባትነት ከተረጋገጠ በኋላም ወርቁ ለልጁ ቀለብ እንዲቆርጥ ለማድረግ ማዕከሉ ለአዜብ ለፍርድ ቤት የሚቀርብ አቤቱታ አዘጋጅቶ ሰጣት። ሆኖም ክሱ በፍርድ ቤት በመታየት ላይ እያለ ወርቁ ልጁን ወስዶ ለማሳደግ ፍቃደኛ መሆኑን ገለፀ። አዜብም የውጭ ሀገር የሥራ ዕድል አግኝታ ለመሄድ የሚያስፈልጋትን ቅድመ ዝግጅት እያጠናቀቀች የነበረ በመሆኑ የልጇ አባት ባቀረበው ሀሳብ ለመስማማት አላመነታችም። ማዕከሉም ይህ መልካም አጋጣሚ የለማን ጥቅምና ደህንነት የሚያስጠብቅ ሆኖ ስላገኘው ጥያቄውን በደስታ ተቀበለው።

በመጨረሻም ማዕከሉ የወላጆቹን ኃላፊነትና ግዴታ በግልፅ የሚዘረዝር ስምምነት አዘጋጅቶ የህፃኑን ወላጆች በማፈራረም ጉዳዩ እልባት እንዲያገኝ አድርጓል።

በአለም አቀፉ የህፃናት መብቶች ስምምነት አንቀፅ 7/1 እና በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገመንግስት አንቀፅ 36/1/ሐ መሰረት ማንኛውም ህፃን ወላጆቹን የማወቅ እና የእነሱንም እንክብካቤ የማግኘት መብት እንዳለው ተደንግጓል።

የሕፃናት ሕጋዊ ከለላ ማዕከል ጥሪ

በዚህ ዕትም ውስጥ ያስነበብናችሁ ታሪኮች ውጤታማ እንዲሆኑ የብዙ ባለሙያችና ተቆርቆሪ የሆኑ ወገኖች ጥረት ይገኝበታል። እያንዳንዳችን በየቤታችን፣ በየጎረቤቶቻችን እንዲሁም በየአካባቢያችን የምናያቸው እና የምንሰማቸው ጥቃቶችና በደሎች እንዲቆሙ የየበኩላችንን ኃላፊነት መወጣት ይኖርብናል።

በቀና መንፈስ እና አስተሳሰብ የሚደረግ ድጋፍ የጥቃት ሰለባ ለሆኑት ህፃናት የሚያስገኘው እፎይታና እርካታ ከፍተኛ መሆኑን ተገንዝበን ህፃናቱን በምንችለው ሁሉ ለመርዳት እንድንገፋፋ ማዕከሉ በህፃናቱ ስም ጥሪውን ያስተላልፋል።

ህፃናትን ልንታደጋቸው የምንችለው ዛሬ የምናየውን እያንዳንዱን ጥቃት ትኩረት በመስጠት ብቻ ነውና ጥቃትን በዝምታ ማለፍ ይብቃ! ህፃናትን እንታደግ! ከስጋትና ከጥቃት ነፃ ሆነው የሚኖሩበትን ህብረተሰብ በጋራ እንፍጠር!